የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ መጋቢት ፬ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.30
ADDIS ABABA 13th March, 2017

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫/፳፻፱ ዓ.ም

ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላት እና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች መወሰኛ (ማሻሻያ) አዋጅ ………………ገጽ ፱ሺ፭፻፹፫

**Contetes**

Proclamation No.1003/2017

Rights and Benefits of Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges (amendment) Proclamation ........................Page 9583

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫/፳፻፱

**ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች ፣ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣የምክር ቤት አባላት እና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላት እና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላት እና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች መወሰኛ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫/፳፻፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፱ሺ፭፻፹፬

**፪. ማሻሻያ**

ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላት እና ዳኞች

## Proclamation No. 1003/2017

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF RIGHTS AND BENEFITS OF OUTGOING HEADS OF STATE AND GOVERNMENT, SENIOR GOVERNMENT OFFICIALS, MEMBERS OF PARLIAMENT AND JUDGES**

WHEREAS, it has become necessary to amend the Rights and Benefits of Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges Proclamation No. 653/2009;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby Proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Rights and Benefits of Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges (amendment) Proclamation No. 1003 /2017".



www.chilot.me

የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፩ (በአዋጅ ቁጥር ፱፻፴፬/፪ሺ፰ እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል ፡-

"፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የስድስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ደመወዝ እየታከለ ይታሰባል፡፡ ሆኖም ጠቅላላ የመቋቋሚያ አበል ክፍያው ከሃያ አራት ወራት ፳፬ ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡ "

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪)ተተክቷል፡-

"፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የሥራ ስንብት ክፍያ ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የስድስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የሚጨረሻው ወር ደመወዝ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤ ሆኖም የሚከፈለው ጠቅላላ የሥራ ስንብት ክፍያ ከአንድ ዓመት ተኩል ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡"

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ እና ፲፮ ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ አንቀጾች ፲፭ እና ፲፮ ተተክተዋል፤

"፲፭. **<u>የመኖሪያ ቤት አበል እና የመኖሪያ ቤት</u>**

፩/ ማንኛውም ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ፡-

ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

፱ሺ፭፻፹፬

ለ) ከአንድ የምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣

የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ ፡-

ሀ) ለሚኒስትር ሲሆን ማነሻው የዘጠኝ ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት

**2. <u>Amendment</u>**

The Rights and Benefits of Outgoing Heads of State and Government, Senior Government Officials, Members of Parliament and Judges Proclamation No. 653/2009 (as amended by Proclamation No. 934/2016) is hereby amended as follows:

1/ Article 13(2) is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

"2/ The amount of maintenance allowance to be paid pursuant to sub-article (1) of this Article shall be equivalent to six month's salary for the first year of service, and one month's salary shall be added for every additional year of service; provided, however, that the total amount of maintenance allowance shall not exceed twenty four (24) month's salary."

2/ Article 14(2) is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

"2/ The amount of severance pay to be paid pursuant to sub-article (1) of this Article shall be equivalent to six month's salary for the first year of service, and one third of the monthly salary shall be added for every additional year of service; provided, however, that the total amount of severance pay shall not exceed one and half year's salary."

3/ Article 15 and 16 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Article 15 and 16:

"15. **<u>Housing Allowance and Residential House</u>**

1/ Any Senior Government Official shall be entitled to housing allowance if he has been released from office:

a) after serving for at least one election term; or

የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ለ) ለሚኒስትር ዴኤታ ሲሆን መነሻው የስድስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሐ) ለምክትል ሚኒስትር ሲሆን መነሻው የአራት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ፳፬ ወራት የመኖሪያ ቤት አበል መብለጥ የለበትም፡፡

፫/ ማንኛውም ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ፡-



ሀ) ቢያንስ ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

ለ) አንድ የምርጫ ዘመን እና ከግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፤

በራሱ ወይም በባለቤቱ ስም የተሠራ የግል መኖሪያ ቤት የሌለው ከሆነ ለራሱና ለቤተሰቡ መኖሪያነት የሚያገለግል ራሱ ኪራይ እየከፈለ የሚኖርበት የመኖሪያ ቤት ይሰጠዋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጠው መኖሪያ ቤት፡-

ሀ) ሚኒስትር ሲሆን ሦስት መኝታ ክፍሎች ያሉት፤

ለ) ሚኒስትር ዴኤታ ወይም ምክትል ሚኒስትር ሲሆን ሁለት መኝታ ክፍሎች ያሉት፤

ይሆናል፡፡

## ፲፮. የተሽከርካሪ አበል እና አገልግሎት

፩/ ማንኛውም ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ፡-

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure upon completing at least half of one election term.

2/ The housing allowance under sub-article (1) of this Article shall be paid in a lump sum and its amount shall be:

a) in the case of a Minister, nine month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

b) in the case of a Minister of State, six month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

c) in the case of a Deputy Minister, four month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

provided, however, that the total payment shall not exceed 24 month's housing allowance.

3/ Any Senior Government Official shall, if he has no private residential house constructed in his own name or in the name of his spouse, be entitled to residential house for himself and for his family, the rent of which shall be covered by himself, if he has been released from office:

a) after serving for at least two election term; or

www.chilot.me

ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

ለ) ከአንድ የምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት የተነሳ፤

የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የተሽከርካሪ አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ ፡-

ሀ) ለሚኒስትር ሲሆን መነሻው የዘጠኝ ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

፱ሺ፭፻፹፯

ለ) ለሚኒስትር ዴኤታ ሲሆን መነሻው የስድስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሐ) ለምክትል ሚኒስትር ሲሆን መነሻው የአራት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ፳፬ ወራት የተሽከርካሪ አበል ክፍያ መብለጥ የለበትም፡፡

፫/ ማንኛውም ሚኒስትር የሆነ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ፡-

ሀ) ቢያንስ ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

ለ) አንድ የምርጫ ዘመን ከግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፤

**አንድ የቤት አውቶሞቢል በመንግሥት ይመደብለታል፡፡**

**፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ለሚመደበው የቤት አውቶሞቢል የአሽከርካሪውን ሹፌር**

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure upon completing at least one and half year of election term.

4/ The residential house to provided under sub-article (3) of this Article shall be:

a) in the case of a Minister it shall be a residential house with three bedrooms;

b) in the case of a Minister of State or Deputy Minister it shall be a residential house with two bedrooms.

**16. Transport Vehicle and Vehicle Allowance**

1/ Any Senior Government Official shall be entitled to vehicle allowance if he has been released from office:

a) after serving for at least one election term; or

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure upon completing at least half of one election term.

2/ The vehicle allowance under sub-article (1) of this Article shall be paid in a lump sum and its amount shall be:

a) in the case of a Minister, nine month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

www.chilot.me

**ደመወዝ ጨምሮ፣ የነዳጅ፣ የጥገና እንዲሁም ሌሎች ወጪዎች በመንግሥት ይሸፈናሉ፡፡**

፩/ ማንኛወም ሚኒስትር ዴኤታ ወይም ምክትል ሚኒስትር የሆነ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊ ፡-



ሀ) ቢያንስ ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፤ ወይም

ለ) አንድ የምርጫ ዘመን ከግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፤

የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የሚከፈለው የተሽከርካሪ አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ ፡-

ሀ) ለሚኒስትር ዴኤታ ሲሆን መነሻው የዘጠኝ ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ለ) ለምክትል ሚኒስትር ሲሆን መነሻው የስድስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ፳፬ ወራት የተሽከርካሪ አበል ክፍያ መብለጥ የለበትም፡፡"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፳ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) እና ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ለ) እና ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክተዋል፤

"**ለ)** ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ ፣ የመኖሪያ ቤት አበል ወይም የመኖሪያ ቤት እና የተሽከርካሪ አበል ወይም የተሽከርካሪ አገልግሎት ለቤተሰቡ ይሰጣል፡፡

**፪/** ማንኛወም ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ከኃላፊነት ተነስቶ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣የቤት አበል ወይም የመኖሪያ ቤትና የተሽከርካሪ አበል

b) in the case of a Minister of State, six month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

c) in the case of a Deputy Minister, four month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

provided, however, that the total payment shall not exceed 24 month's vehicle allowance.

3/ Any Senior Government Official shall be provided by the Government with one sedan automobile vehicle if he is a Minister and has been released from office:

a) after serving for at least two election term; or

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure upon completing at least one and half election term.

4/ For the sedan automobile vehicle provided pursuant to sub-article (3) of this Article, the running costs of the vehicle including driver's salary, fuel, maintenance and other costs, shall be covered by the Government.

5/ Any Senior Government Official shall be entitled to vehicle allowance if he is a Minister of State or Deputy Minister and has been released from office:

a) after serving for at least two election term; or

፱ሺ፭፻፹፱

ወይም የተሽከርካሪ አገልግሎት ለቤተሰቡ ይሰጣል፡፡ ”

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ርዕስ እና ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) ያሉት ድንጋጌዎች ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ርዕስና ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) ተተክተዋል፤ እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፬) ተጨምሯል

"**፳፬. <u>የቤት አበል እና የመኖሪያ ቤት አገልግሎት</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተለይ ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር የተፈቀደው የቤት አበል ወይም የመኖሪያ ቤት አገልግሎት ከኃላፊነት ለተነሳ አፈጉባኤ፣ የመንግሥት ዋና ተጠሪና ተቃዋሚ ፓርቲ መሪም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተለይ ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር ደኤታ የተፈቀደው የቤት አበል ወይም የመኖሪያ ቤት አገልግሎት ከኃላፊነት ለተነሳ ምክትል አፈጉባኤ፣ ምክትል የመንግሥት ተጠሪና ተቃዋሚ ፓርቲ መሪም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተለይ ከኃላፊነት ስለተነሳ ምክትል ሚኒስትር የተፈቀደው የቤት አበል ወይም የመኖሪያ ቤት አገልግሎት ከኃላፊነት ለተነሳ ረዳት የመንግሥት ተጠሪና ተቃዋሚ ፓርቲ መሪም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፫(፬) (ለ) ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች በተለይ ከኃላፊነት የተነሳ ሚኒስትር ደኤታ ወይም ምክትል ሚኒስትር የተፈቀደው የመኖሪያ ቤት አገልግሎት ፡-

ሀ ሁለት የምርጫ ዘመን ወይም ከዚያ በላይ ላገለገሉ የምክር ቤት አባላትም ተፈፃሚ ይሆናል፤

፱ሺ፭፻፺

ለ አንድ የምርጫ ዘመንና ከግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፤

በራሱ ወይም በባለቤቱ ስም የግል መኖሪያ

b) due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure upon completing at least one and half election term.

6/ The vehicle allowance under sub-article (5) of this Article shall be paid in a lump sum and its amount shall be:

a) in the case of a Minister of State, nine month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

b) in the case of a Deputy Minister, six month's full payment for the initial service and an addition of half of the monthly payment for every additional year of service beyond the first election term;

provided, however, that the total payment shall not exceed 24 month's vehicle allowance.

4/ Paragraph (b) of sub-article (1) and sub-article (2) of Article 20 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new paragraph (b) and sub-article (2):

"b) the resettlement allowance, severance pay, housing allowance or residential house and vehicle allowance or transport vehicle that may have been due to him had he been released from office shall be paid to his family.

2/ If an Ex-Senior Government Official dies, before he has received his benefits, the resettlement allowance, severance pay, housing allowance or residential house and vehicle allowance or transport vehicle that have been due to him shall be paid to his family."

www.chilot.me

ቤት የሌለው ከሆነ ለራሱና ለቤተሰቡ መኖሪያነት የሚያገለግል ራሱ ኪራይ እየከፈለ የሚገለገልበት የመኖሪያ ቤት ይሰጠዋል፡፡

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፭ ርዕስ እና ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ርዕስና ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤

"፳፭.**<u>የተሽከርካሪ አገልግሎት እና አበል</u>**

፩/በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ከኃላፊነት ስለተነሱ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በተለይ ከኃላፊነት ስለተነሳ ሚኒስትር የተፈቀደው አንድ የቤት አውቶሞቢል አገልግሎት ወይም የተሽከርካሪ አበል ከኃላፊነት ለተነሳ አፈጉባኤ፣ የመንግሥት ዋና ተጠሪና ተቃዋሚ ፓርቲ መሪም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡"

፯/ የአዋጁ አንቀፅ ፳፱ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲሰ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተተክቷል፤

"፪ ከኃላፊነት የተነሳው የምክር ቤት አባል ቀድሞ በነበረበት የመንግስት መ/ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሠረት ሊመደብ ካልቻለ በሌላ የመንግስት መ/ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት በሚገኝ ተመሳሳይ ከፍት የሥራ ቦታ ላይ ይመደባል፡፡"

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) እና ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ለ) እና ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተከተዋል፤

"**ለ)** ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ ፣ የመኖሪያ ቤት አበል ወይም የመኖሪያ ቤት አገልግሎት እና የተሽከርካሪ አበል ወይም የተሽከርካሪ አገልግሎት ለቤተሰቡ ይሰጣል፡፡

፱ሺ፭፻፹፱

፪/ ማንኛውም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ተነስቶ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ ፣ የመኖሪያ ቤት አበል ወይም የመኖሪያ ቤት አገልግሎት እና የተሽከርካሪ አበል ወይም የተሽከርካሪ አገልግሎት ለቤተሰቡ ይሰጣል፡፡ "

፫. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፴ ቀን **፪ሺ፱** ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5/ The title and sub-article (1) to (3) of Article 24 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new title and sub-article (1) to (3); and also new sub-article (7) is added:

"24. **<u>Housing Allowance and Residential House</u>**

1/ The provisions of Article 15 of this Proclamation providing for housing allowance or residential house to Ex-Senior Government Officials, specifically to an Ex-Minister shall also be applicable to an Ex-Speaker, Chief Government Representative and Opposition Party Leader.

2/ The provisions of Article 15 of this Proclamation providing for housing allowance or residential house to Ex-Senior Government Officials, specifically to an Ex-Minister of State shall also be applicable to an Ex-Deputy Speaker, Deputy Government Representative and Opposition Party Representative.

3/ The provisions of Article 15 of this Proclamation providing for housing allowance or residential house to Ex-Senior Government Officials, specifically to an Ex-Deputy Minister shall also be applicable to an Ex-Assistant Government Representative and Assistant Opposition Party Representative."

7/ Residential house allowded for Ex-sinier government officials especially for Ex-Miniter of state or Ex-Deputy Minister in paragraph (b) of Article 15 (4) of this Proclamation shall be Provided:

a) For Ex-members of parliament serving two or more election terms;

www.chilot.me

b) Due to sickness, disability or any other ground caused by force majeure upon completing atleast one and half of election term;

for himself and his family, the rent of which shall be covered by him. If he has no privet residential house in his own name or the name of his spouse.

6/ The title and sub-article (1) of Article 25 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new title and sub-article (1):

**"25. <u>Transport Vehicle and Allowance</u>**

1/ The provisions of Article 16 of this Proclamation providing for one sedan automobile vehicle or transport allowance to Ex-Senior Government Officials, specifically to an Ex-Minister shall also be applicable to an Ex-Speaker, Representative of Government and Opposition Party Representative."

7/ Article 29(2) is delated andreplaced by the following new sub-article (2)

"2" if Ex-member of parliament who has been released from office could not be reinstated in accordance with sub-article (1) of this article, he will be assigned to a similar vacant job in any other government office or public enterprise.

8/ Paragraph (b) of sub-article (1) and sub-article (2) of Article 31 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new paragraph (b) and sub-article (2):

"b) the resettlement allowance, severance pay, housing allowance or residential house and vehicle allowance or transport vehicle that may have been due to him had he been released from office shall be paid to his family.

አዲስ አበባ መጋቢት ፬ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

www.chilot.me

2/ If an Ex-member of parliament dies, before he has received his benefits, the resettlement allowance, severance pay, housing allowance or residential house and vehicle allowance or transport vehicle that have been due to him shall be paid to his family.”

**3. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force as of 9th November, /2016.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of March, 2017**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me